# ‘ሕግ ይከበር! በሃይማኖት መነገድ ይቁም!” ህዝበ ሙስሊሙ

ከሲኢድ መሃመድ

የእስልምና ሃይማኖት አማኞችን በሚመለከት የተለያዩ ሚዲያዎች በቋሚነት የተላያዩ ዘገባዎችን እየያዙ  መውጣት ከጀመሩ በርከት ያሉ ወራት ተቆጥረዋል፡፡ ዘገባዎቹ በአመዛኙ ህዝበ ሙስሊሙን የሚያረጋጉና ለዘመናት ይዞት የዘለቀውን መቻቻልና ወንድማማችነቱን አጥብቆ እንዲይዝ የሚመክሩ ሳይሆኑ በመካከሉ የተፈጠረውን መቃቃርና ግጭትን የሚያባብሱና የሚያሰፉ ናቸው፡፡  በእስልምና ሃይማኖት ስም የሚታተሙ  እና ሌሎች ሃይማኖታዊ ያልሆኑ  በርካታ የግል ጋዜጦች በተደጋጋሚ በዚሁ ዙሪያ የተለያዩ አፍራሽ ዘገባዎችን እያየዙ  በመውጣት ላይ ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚወጡት ጽሁፎችን በአንክሮ ለሚያነብ ሰው የሚሰጡት መልእክት ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ነጻነት አለመኖሩን ነው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ወደ አመጽና ብጥብጥ እንዲገባ ለማድረግ የሚገፋፉና በሃይማኖት ስም የህዝቡን ቀናኢ ልቦና ለመስለብ ያለሙ በመሆናቸው በአገራችን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ያለወቀ ሰው ቢደናገር እምብዛም አያስገርምም፡፡

ከሁለት አሰርት ዓመታት በፊት በአገራችን የነበረው ስርዓት የአፈና  ነበር፡፡ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያው መብት የማይከበርበት የሃይማኖት ነጻነት የታፈነበት ስርት ነበር፡፡ አሁን በአገራችን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን በልማት ምህዋር ላይ የመሽከርከር፤የተረጋጋ ሰላምና የህዝብ ሕብረት መጠናከር ብሎም የአንድነት፤ የመከባበርና የመቻቻል ነው፡፡ ኢትዮጵያ የህግ የበላይነት የሰፈነባት፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት እና  የሃይማኖት ነጻነት የተረጋገጠባት አገር ናት፡፡
ሃይማኖትን ማራማድ እንደ ትልቅ የፖለቲካ ወንጀልና ክህደት የሚቆጠርበት ያ ክፉ ዘመን ዛሬ የጭራው ጫፉም የለም፡፡ አማኞች ሃይማኖታዊ ተልእኮአቸውን ለመፈጸም የሚሸማቀቁበት፤ በጋራ ተሰባስበው ሃይማኖታዊ ተልእኮአቸውን መወጣት የማይችሉበት፤ የማምለኪያ ስፍራቸው የማይከበርበት፤ ካድሬዎችና ፖለቲከኞች  እየገቡ ስጋትና ሁከት የሚፈጥሩበት ዘመን አክትሟል፡፡ ያ ሁሉ የሃይማኖት ነጻነት አፈና ባከተመበትና ህዝቦች የፈለጉትን ዓይነት ሃይማኖት በነጻነት ለማምለክና ሃይማኖታዊ ተልእኮአቸውን ያለምንም መሸማቀቅ እና ስጋት ለመፈጸም በተቻለበት በአሁኑ ወቅት  ሃይማኖት ነክ ጥያቄ የሚነሳበት ምህዳር እጅጉን የቀጨጨ ነው።።

ሼሕ አህመዲን ይባላሉ፡፡ በስልሳዎቹ የእድሜ ክልል ይገኛሉ፡፡ በአንዋር መስጊድ ግቢ ነበር ያገኘኋቸው፡፡ ለመሆኑ ይህ አሁን በህዝበ ሙስሊሙ መካከል እየተፈጠረ ያለው ነገር ምንድንነው? አልኳቸው፡፡ ሼሕ አህመዲንም እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ፡፡

‘በአሁኑ ወቅት የሃይማኖት ነጻነታችን ተከብሯል፡፡ በህዝበ ሙስሊሙ መካከል እየተነሳ ያለው መከፋፈል ሃይማኖታዊ ጥያቄ ያዘለ አይደለም፡፡ የእስልምና አማኞችን እርስበርስ በማፋጀት ሃይማኖታችንን ለመበተን የተወጠነ አጀንዳ ነው፡፡ ይህ ከህዝበ ሙስሊሙ የተሰወረ ነገር አይደለም፡፡ እኔም እንደ ሙስሊምነቴ የምገነዘበው ነገር ይኸው ነው፡፡ ይህ ሁላችንም የምንመሰክረው ሃቅ ነው፡፡ ምስክርነታችን ደግሞ ለአላህ እንጂ ለሰዎች አይደለም፡፡”

ታዲያ ሕገወጥነት በህዝበ ሙስሊሙ ስም መፈጠሩ በእውነቱ የሚያሳስብ ነገር ነው፡፡ ሁሉም ሃይማኖቶች በአማኞቻቸው ዘንድ የተቀደሱ ናቸው፡፡ የሃይማኖት የበላይና የበታች ሳይኖር ሁሉም ለሚመለከታቸው መእመናን የሚኖራቸው ክብደት እኩል ነው፡፡ በመሆኑም የእስልምና ሃይማኖት የተቀደሰና የተባረከ ሃይማኖት ነው፡፡ ሁሉም ህዝበ ሙስሊም ለሃይማኖቱ ቀናኢና የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችን ነጻነት አክባሪ ነው፤፤ ህዝበ ሙስሊሙ ህግ አክባሪና ለሕግ ተገዥ ነው፡፡ ሃይማኖታዊ መጽሃፉ የሚያስተምረውም ከዚሁ የተለየ አይደልም፡፡

ሰውን ግደል! ደም አፋስ! እርስ በርስ ተበጣበጥ ተፋጅ! የሚል አስተምህሮት ፈጽሞ የለም፤፤ በቁርአናችን ውስጥም አልሰፈረም፡፡ ሰላም፣ ፍቅር፣ መከባበርና መቻቻልን ነው የእስልምና ድርሳናት የሚያስተምሩት፤፤ የሃይማኖት አባቶቻችንም ከዚህ የተለየ ነገር አላስተማሩንም፡፡ እስካሁን በህዝበ ሙስሊሙመካከል ያለውም ከዚህ የተለየ ነገር አይደለም፡፡ ለዘመናት የዘለቀው መቻቻልና መተሳሰብ የዚሁ ነጸብራቅ ነው፡፡

ራስን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ እሱ በአላህ ዘንድ ዝቅ ይላል ፡፡ ብጹእ እኔ ነኝ የሚል ራሱን የማያውቅ አላህንም የማያውቅ ነው፡፡ የአላህን ምሉዕነት የማይገነዘብ ነው፡፡ የእኔን አምልኮ ብቻ ተከተሉ የሚሉ አማኞችም ከአላህ መስመር የወጡ ናቸው፡፡ ከእብሪተኝነትና ከጽንፈኝነት የሚመነጭ ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖትን የሚጻረር ነው፡፡ ብጹእ አንድ አላህ ብቻ ነው፡፡

በርካታ የሙስሊሙ ህብረተሰብ አባላት የሚገለጹትም ከዚሁ የተለየ አይደለም፡፡ “ሃይማኖታችን የሚያስተምረው ሰላም፣ ፍቅርና ተስፋን ነው፡፡ አገራዊ ክህደትንና ሕገወጥነት የሚያደፋፍር አስተምህሮት የለውም፡፡ አሁን በተቀደሰው ሃይማኖታችን ስም እየተፈጸመ ያለው ደባ መንግስት አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ በመውሰድ ሕግ ሊያስከብርልን ይገባል፡፡ ሕግ ይከበር! በሃይማኖት መነገድ ይቁም!” የሚል ነው፡፡

በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚኖሩ የእስልምና ሃይናኖት አማኞች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህዝበ ሙስሊሙ መካከል መከፋፈልና ብጥብጥን ለማስከተል እየተሸረበ ያለውን ሴራ ምንነትና በአፈታቱ ዙርያ ከሚመለከታቸው የየአካባቢው የህብረተሰብ አባላት፣ መስተዳድሮችና የፀጥታ ጉዳይ ሃላፊዎች ጋር በተደረጉ የምክክር መድረኮች ላይ ህዝበ ሙስሊሙ በአንክሮ ያሳሰበውም ‘ሕግ

ይከበር! ፖለቲካና ሃይማኖት የተለያዩ ነገሮች ናቸውና በተቀደሰው ሃይማኖታችን ስም መነገድ ይቁም!" የሚል ነው፡፡

የህዝበ ሙስሊሙ ወኪሎች እና የህዝበ ሙስሊሙን ጥያቄ ለመንግስት የሚያቀርቡስ እነማን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ ላይ መግባባት ተደርሷል፡፡ ተወያዮች እንዳስመሩበት ህዝበ ሙስሊሙ አግባብነት ያለው ጥያቄ አቅርቦ ምላሽ ያላገኘበት ወቅት የለም፡፡ በአገራችን ያለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይህንን ለማስተናገድ የሚያስችል ነው፡፡ ይሁንና ጥያቄዎቻችን ለመንግስት መቅረብ ያለባቸው ህዝበ ሙስሊሙ በወከላቸው የእስልምና ሃይማኖት አማኞች እንጂ በፖለቲከኞች ሊሆን አይገባም፡፡

ፖለቲከኞች ድብቅ ዓላማቸውን በየተቀደሰው ሃይማኖታችን ስም ለማራመድ መሞከራቸው ህዝበ ሙስሊሙን ያስቆጣ ጉዳይ ነው፡፡ የተቀደሰው ሃይማኖታችን ስለምን የአክራሪዎችና የከሰሩ ፖለቲከኞች መነገጃ ይሆናል? ሕግ ይከበርልን አመጸኞች ለሕግ ይቅረቡልን የሚል ጥያቄ ለመንግስት ያቀረቡት የህዝበ ሙስሊሙ አባላት መንግስት ሚወስደውን ማንኛውም ሕጋዊ እርምጃ እንደሚደግፉ ነው የገለጹት፡፡

በህዝበ ሙስሊሙ መካከል እየተነሳ ያለው ጥያቄ ሕግን ማን ያስከብር? የሚል ነው፡፡ መልሱ በሕገ መንግስቱ ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ከመንግስት ዋነኛ ተግባራት አንዱ የሕግን የበላይነት ማስከበር ነው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙም እየጠየቀ ያለው ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ህግን የማስከበር ስራው አሁንም ህዝበ ሙስሊሙን ለመበተን አልሞ በተነሳው ሕገወጥነት ላይ እንዲተገበር ነው፡፡ መንግስት ይህንን ሕገወጥነት ፈር ለማስያዝ ለሚወስደው ማንኛውም ዓይነት ሕጋዊ እርምጃ ህዝበ ሙስሊሙና ሌላውም የህብረተሰብ ክፍል ከመንግስት ጎን ሊሰለፍ ይገባል፡፡ አሁን በጠጨባጭ እየሆነ ያለውም ይህ ነው፡፡

ሼሕ መሐመድ ነዋሪነታቸው በደሴ ከተማ ሲሆን የ65 ዓመት አዛውንት ናቸው፡፡ በህዝበ ሙስሊሙ መካከል እየተፈጠረ ያለው የእርስ በርስ ብጥብጥና ሁከት መነሻውን በተመለከተ እንዲህ ነበር ያጫወቱኝ፡፡ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በእስልምና ስም በአንዳንድ ኃይሎች አነሳሽነት እየታየ ያለው እንቅስቃሴ ሃይማኖታዊ መሰረት የለውም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን ጥያቄ ለመመለስ የሚቻለው የእስልምና አስተምህሮትንና አሁን በእነዚህ ቡድኖች እየተነሳ ያለውን የጽንፈኝነት ተግባር በንጽጽር በማየት ይሆናል፡፡ እነዚህ ቡድኖች የሚሰብኩት ምንድን ነው? እኛ ከምንከተለው አምልኮት ውጪ ሌላ የእስልምና አምልኮት የለም የሚል ነው፡፡ ሙስሊሙ በሙሉ እኛ የምንከተለውን እምነት መከተል ይኖርበታል ከዚህ ውጪ ሌላ እምነት በአገሪቱ መኖር የለበትም የሚል በመሆኑ ይህ በፍጹም ተቀባይነት አይኖረውም ነበር ያሉኝ፡፡

የሌላ አስተምህሮ ተከታዮች መስበክና ማስተማር ያቁሙ፤ ለዚህ ደግሞ መንግስት እርምጃ ይውሰድልን የሚል ነው፡፡ በሌላም በኩል  እኛ ከምንከተለው አስተምህሮና እምነት ውጭ ያሉ የሌላ እምነት ተከታዮችን ማሳደድና ማጥፋት የጽድቅ ተግባር በመሆኑ ይህንንም መፈጸም ተገቢ ነው የሚል የጽንፈኝነት አመለካከት የሚንጸባረቅበት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር  ይህ ቡድን የእርስ በርስ ግጭትንና ብጥብጥን የሚሰብክ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮት ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ፍቅር፣ ሰላምና አንድነትን ያስተምራል፡፡ ጠላትህን እንደራስህ መውደድንና ሁሉም ነገር ለአላህ መስጠትን፣ ብቀላ ማስወገድን ነው የሚያስተምረው፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሁለት ገጽታዎች በእጅጉ የተለያዩ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው የእነዚህ ቡድኖች እንቅስቃሴ ሃይማኖታዊ ተልእኮ የለውም የምንለው፡፡

የእስልምና ሃይማኖት አማኝ ለሃይማኖቱ ቀናኢ ለሰዎች ህይወት የሚራራና የሚያስብ ሰላምን የሚመርጥ ህዝብ ሆኖ እያለ የእነዚህ  ቡድኖች እንቅስቃሴ ግን ከዚህ ያፈነገጠ ነው፡፡ ከዚህ እምነት አፈነገጡ ማለት ትክክለኛ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ሳይሆኑ ህዝበ ሙስሊሙን ለመበተንና እርስ በርስ ለማፋጀት ብሎም የእስልምና ሃይማኖትን ለማዳከም የተነሱ ናቸው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ይህንን እየተገነዘበው መጥቷል፡፡ ሃይማኖቱን ለማጥፋት  ታጥቀው የተነሱ ቡድኖች በሃይማኖቱ ስም እየነገዱ መሆኑንም በሚገባ ተረድቶታል፡፡ ጽንፈኞቹ የእስልምና ሃይማኖትን ለማጥፋት ታጥቀው የተነሱ ለመሆናቸው ከምግባራቸው ለማወቅ ችሏል፡፡

ሶፊያ አህመድ የ35 ዓመት ወጣት ነች፡፡ ነዋሪነቷ በአዲስ አበባ ሲሆን ስራዋም የህግ ጥብቅና ነው፡፡ ሶፊያም ተመሳሳይ ሐሳብ አላት፡፡ ‘እስልምና ሰላም፣  ፍቅር፤ወንድማማችነት፡መተሳሰብና አብሮነት ነው፡፡ ግጭትን፡የእርስ በርስ መፋጀትንና መበላላትን አያስተምርም፡፡ አሁን ያለው ጉዳይ በሃይማኖት የተሸፈነ የፖለቲካ ጉዳይ ነው፡፡ ሃይማኖትን ለመሳሪያነት የመጠቀም ሁኔታ ነው በተጨባጭ እየታየ ያለው፡፡ይህም ህግን የመተላለፍ እንቅስቃሴ ነው በማለት አጫውታኛለች፡፡

ሕገመንግስቱ የሃይማኖት ነጻነትን አረጋግጧል፡፡ በሕገመንግስቱ የተሰጠን መብት ማንም ቡድን እየተነሳ ሊያፈርሰውና የህዝብን ነጻነት ሊያውክ ሰላማቸውን ሊያደፈርስ የሚችልበት ሁኔታ ክፍት ሊሆን አይገባም፡፡ ይህ ጉዳይ ህገመንግስቱን የማስጠበቅና የማስከበር ጉዳይ  በመሆኑ ይህ በዋናነት መንግስት የሚፈጽመው ሆኖ ህዝበ ሙስሊሙና ሌላው ሕብረተሰብም ከመንግስት ጎን ቆሞ እነዚህን ነውጠኞች እያጋለጠ የሚሰጥበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርባታ፡፡”

ሶፊያ አያይዛም ‘መላው ህዝበ ሙስሊም የእነዚህ ግለሰቦች ወይም ቡድን እንቅስቃሴ ሃይማኖታቀዊ ተልእኮ  እንደሌለውና እንዲያውም ህዝበ ሙስሊሙን በማበጣበጥና የእርስ በርስ ደምመፋሰስ በመፍጠር የእስልምና  ሃይማኖት  አማኞችን በመበተን ሃይማኖተን ማጥፋትና በአክራሪና ጽንፈኛ እምነት መተካት  መሆኑን ትናገራለች፡፡

በአገሪቱ ሕገመንግስት በግልጽ እንደሰፈረው የሕግን የበላይነት ማስከበር ሰላምንና መረጋጋትን ማስፈን የመንግስት ሃላፊነት ነው፡፡ መንግስት የሙስሊሙን ሕብረተሰብ ጥያቄ በመቀበል ጽንፈኞችን መስመር ሊያስይዝ ይገባል፡፡ መንግስት ሕገመንግስቱን ለማስከበርና የህዝበ ሙስሊሙን ሰላምና ነጻነት ለመጠበቅ በጽንፈኞች ላይ ያላሳለሰ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡

በአገራችን ለዘመናት የዘለቀውን በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሰረጸውንም የእርስ በርስ ፍቅርና መተጋገዝ ለመናድና ለመሸርሸር፣ የእስልምና ሃይማኖት አማኞችን ከሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ጋር የማያባራ የሃይማኖት ግጭት ውስጥ ለማስገባትና የአገሪቱን ሰላምና ልማት ለማደናቀፍ በእንቅስቃሴ ላይ ያሉትን ጽንፈኞች ወደ ሕግ መስመር ማስገባት ጊዜ የሚሰጠው ተግባር አይደለም፡፡

ይህ በህዝበ ሙስሊሙ መካከል በጥቂት የዋህቢያ እመነት ተከታዮች ስም የሚንቀሳቀሱ ህቡእ ተልኮ ያላቸው ሰዎች እየተፈጸመ ያለው ድርጊት ለህዝበ ሙስሊሙ በከፋ ደረጃ ተጎጂ የሚያደርግና በሚፈጠረው የእርስ በርስ ግጭትና በግርግር የተወሰኑ የጥፋት መልእክተኞችን እኩይ ዓላማ ለማሳካት ያለመ ነው፡፡ የአልሸባብንና የአልቃይዳን እኩይ ዓላማና ተልዕኮ ያነገበና አገራችንን ወደኋላ ለመጎተት ያለመ ተግባር ነው፡፡

በተለያዩ የሚዲያ አውታሮች መንግስት ሕግን ለማስከበር የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በማጋነንና ሕብረተሰቡን ማደናገር በሚችሉ ዘገባዎች በማጀብ በግርግር ስውር ዓላማቸውን ለማሳካት አክራሪዎች የሸረቡት ሴራ እንጂ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብን የሚመለከት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ እንደዚህ ዓይነት አጀንዳ የለውም፡፡ ህብረተሰቡ እርስ በርሱም ሆነ ከሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በሰላምና በፍቅር መኖርን ነው የሚመርጠው፡፡ ለዘመናት ይዞት የመጣው ባህሪም ይኸው ነው፡፡

የኢትዮጵያ ልማት የሚያስደነግጣቸው የውጭና የውስጥ ሃይሎች እጅ እንዳለበት የተለያዩ መረጃዎች የሚጠቁሙት ይህ በህዝበ ሙስሊሙ መካከል ተከስቶ ያለው ብጥብጥና ግጭት የሚገታው በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ተሳትፎ ብቻ አይሆንም፡፡ ይህ የተቀናጀ ትግል ያስፈልገዋል፡፡

ሙስሊሙ ህብረተሰብም ከዚህ የተለየ ጥያቄ የለውም፡፡ ጥያቄው የሕግ የበላይነት ይከበር ነው፣ በተቀደሰው የእስልምና ሃይማኖት ስም መነገድ ይቁም ነው፡፡ ጥያቄያቸው በሕገመንግስቱ የተሰጠን የሃይማኖት ነጻነት መብት አክራሪ ቡድኖች ሊነፍጉንና ይህንን እመን ይህንን አትከተል ሊሉን ሊያግዱን ሊያስፋራሩንና ለብጥብጥና ለሁከት ሊዳርጉን አይገባም የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ መሰረታዊ ጥያቄ ነው፡፡ በአገራችን ሕግ መከበር አለበት፡፡ ሁሉም እንቅስቃሴ ሕገመንግስቱን አክብሮ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ ደንበር አልፈው በሃይማኖት ስምም ሆነ በሌላ መልክ

**የሚንቀሳቀሱ ቡድኖችና ግለሰቦች ሕገወጥ በመሆናቸው ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ሕግ ይከበር! በሃይማኖት ስም መነገድ ይቁም!**